ህያው ክርስቶስ

የሐዋርያት ምስክርነት

የኋለኛው ቀን ቅዱሳን የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን

እየሱስ ክርስቶስ ከሁለት ሺህ አመታት በፊት የተወለደበትን ሰናከብር፣ እቻ ሰለሌለው ሕይወቱ እውነነት እና ሰለእርሱ ታላቅ የኃጢያት ክፍያ መሰዋዕት ወሰን የለሽ በጎነት እንመሰክራለን። በምድር ላይ በኖሩት እና ገና በሚኖሩት ላይ እንዲህ ያለ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ ማንም የለም።

እርሱም የብሉይ ኪዳን ታላቁ ያህዌህ እና የአዲሰ ኪዳን መሲህ ነበር። በአባቱ ትዕዛዝ መሠረት ምድርን የፈጠረው እርሱ ነበር። “ሁሉ በእርሱ ሆነ ከሆነውም እንዳች ሰንኳ ያለ እርሱ አልሆነም” (ዮሐንሰ 1፥3)። ምንም እንኳን ኃጢያት የሌለበት ቢሆንም፣ ጽድቅን ሁሉ ይፈጽም ዘንድ ተጠመቀ። “መልካም እያደረገ … ዞረ” (የሐዋርያት ሰራ 10፥38)፣ ይሁን እንጂ በዚህም ተነቀፈ። ወንጌሉ የሠላም እና የበጎ ፈቃድ መልእክት ነበር። ሁሉም ምሳሌውን ይከተሉ ዘንድ ተማነጸ። በሽተኞችን እየፈወሰ፣ ለእውሮች ብርሀንን እየሰጠ፣ እና ሙታንን እያሰነሳ በፍልሰጤም መንገዶች ተመላለሰ። የዘለአለም እውነቶችን፣ በቅድመ ምድር የመኖራችንን እውነታ፣ የምድራዊ ህይወታችንን ዓላማ፣ እንዲሁም የእግዚአብሔር ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በሚመጣው ህይወት ሊኖራቸው ሰለሚችለው አቅም አሰተምሯል።

ለታላቅ የኃጢያት ክፍያ መሥዋዕቱ ማሰታወሻ ይሆን ዘንድ ቅዱሰ ቁርባንን መሰረተ። እርሱም በሀሰት ክሶች ተይዞና ተወግዞ፣ ህገወጥ ሰዎች ደሰ ይሰኙ ዘንድ ተፈርዶበት እና በቀራንዮ በመሰቀል ላይ ይሞት ዘንድ ተፈርዶበት ነበር። ለሰው ዘር ሁሉ ኃጢያት ቤዛ ይሆን ዘንድ ህይወቱን ሰጠ። በምድር ላይ ለኖሩት እና ለሚኖሩት ሁሉ የተሰጠ የውክልና ሰጦታ ነበር።

ለሰው ልጆች ሁሉ ታሪክ ማዕከል የሆነው ህይወቱ በቤተልሔም እንዳልተጀመረ እና በቀራንዮ እንዳላበቃ በክብር እንመሰክራለን። እርሱ የአብ የበኩር ልጅ፣ በሰጋ የተገለጠ አንድያ ልጅ፣ የአለም አዳኝ ነበር።

“ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ” ከመቃብር ተነስቷል (1 ቆሮንቶስ 15፥20)። ከሞት እንደተነሳም ጌታ፣ በህይወት ዘመኑ የወደዳቸውን ጎበኘ። ደግሞም በጥንታዊ አሜሪካ ውሰጥ ይኖሩ በነበሩት በእርሱ “ሌሎች በጎች” መሐል (ዮሐንሰ 10፥16) አገለገለ። በዘመናዊው አለምም፣ እርሱ እና አባቱ ለረጅም ጊዜ ተሰፋ የተደረገበትን “የዘመናት ፍጻሜን” (ኤፌሶን 1፥10) በማሰተዋወቅ ለብላቴናው ጆሴፍ ሰሚዝ ተገለጡ።

ህያው ክርስቶሰን በተመለከተ ነቢዩ ጆሴፍ ሰሚዝ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ፤ የራሱ ጠጕርም እንደ ንጹህ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ ፊቱም ከብርቱ የጸሀይ ብርሀን በላይ የሚያበራ ነበር፤ ድምፁም እንዲህ የሚል እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ፣ እንዲሁም የያህዌህ ድምፅ ነበር፦

“እኔ ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ፤ እኔ ህያውም ነኝ፣ የተገደልኩትም እኔ ነኝ፤ እኔም በአብ ዘንድ አማላጃችሁ ነኝ” (ት. እና ቃ. 110፥3–4)።

በተጨማሪም ነቢዩ ሰለእርሱም እንዲህ አውጇል፦ “እናም አሁን፣ ሰለ እርሱ ከተሰጡት ብዙ ምስክሮች በኋላ፣ ይህም በመጨረሻ ሰለ እርሱ የምንሰጠው ምስክርነት፦ እርሱ ህያው መሆኑን ነው!

“በእግዚአብሔር ቀኝ አይተነዋልና፤ እናም እርሱ የአብ አንድያ ልጅ እንደሆነም ሲመሰክርም ድምፅ ሰምተናል—

“አለማትም በእርሱ፣ እናም በእርሱም አማካይነት፣ እናም ከእርሱም ዘንድ ናቸው እናም ተፈጥረዋል፣ እናም ነዋሪዎችዋም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው” (ት. እና ቃ. 76፥22–24)።

እኛም የእርሱ ክህነት እና ቤተክርስቲያኑ “በሐዋርያት እና በነቢያት መሠረት … [ታንጸው]፣ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ [ሆኖ]” (ኤፌሶን 2፥20) በምድር ላይ በዳግም እንደተመለሱ በክብር እናውጃለን።

አንድ ቀን ወደ ምድር እንደሚመለሰም እንመሠክራለን። “የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል፣ ሥጋ ለባሹም ሁሉ በአንድነት ያየዋል” (ኢሳይያስ 40፥5)። እንደ ነገሰታት ንጉሰ ይገዛል እናም እንደ ጌቶች ጌታ ይነግሳል፣ ጉልበትም ሁሉ ይንበረከካል ምላሰም ሁሉ በእርሱ ፊት በአምልኮ ይናገራል። እያንዳንዳችንም እንደ ሥራችን እና እንደ ልባችን መሻት በእርሱ ይፈረድብን ዘንድ እንቆማለን።

በእርሱ በትክክል እንደተሾምን ሐዋርያት፣ ኢየሱስ ህያው ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር የማይሞት ልጅ እንደሆነ እንመሰክራለን። እርሱም ዛሬ በአባቱ ቀኝ የሚገኘው ታላቅ ንጉሰ አማኑኤል ነው። እርሱም የዓለም ብርሃን፣ ህይወት እና ተሰፋ ነው። የእርሱም መንገድ በዚህ ዓለም ወደ ደሰታ እና በሚመጣው አለም ወደ ዘለዓለማዊ ህይወት የሚመራ ነው። ወደር የለሽ ለሆነ መለኮታዊ ልጁ ሰጦታ እግዚአብሔር ይመሰገን።

ቀዳሚ አመራር

Gordon B. Hinckley
Thomas S. Monson
James E. Faust

ጥር 1 ቀን 2000 (እ.አ.አ)

የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ቡድን

Boyd K. Packer
L. Tom Perry
David B. Haight
Neal A. Maxwell
Russell M. Nelson
Dallin H. Oaks
M. Russell Ballard
Joseph B. Wirthlin
Richard G. Scott
Robert D. Hales
Jeffrey R. Holland
Henry B. Eyring

Unofficial poster layout of the text published on churchofjesuschrist.org. Not an official publication of The Church of Jesus Christ of Latter-day Saints. Generated by Urim, urim.samuelbaird.com